የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 23 እና 24

1. አይሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በጲላጦስ ፊት ምን ብለው ከሰሱት?
ሀ)ለቄሣር ግብር እንዳይሰጥ ከልክሏል
ለ)ሕዝቡን አሳምጿል
ሐ)ራሱን የእስራኤል ንጉሥ አድርጓል
መ)ሁሉም

2. ጲላጦስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለምን ወደ ሄሮድስ ላከው?
ሀ)የገሊላ ሰው መሆኑን ሲያውቅ
ለ)ከእራሱ የተሻለ ፍርድ ይሰጣል ብሎ በማሰብ
ሐ)ሄሮድስን እጅግ ስለሚወደው
መ)ሁሉም

3. ሄሮድስ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ሲያይ
ሀ) በጣም አዘነ
ለ) ሊያየው ይመኝ ነበረና ደስ አለው
ሐ)ከጲላጦስ ዘንድ ስለመጣ ተበሳጨ
መ)ሁሉም

4. ሄሮድስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ጲላጦስ ሲያስመልሰው
ሀ)የሚያንፀባርቅ ልብስ አልብሶት ነበር
ለ)ደግሞ ደጋግሞ መርምሮት ነበር
ሐ)አቃሎት አፊዞበት ነበር
መ)ሁሉም

5. በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ጉዞ ላይ በማቴዎስ ወንጌል ያለው ታሪክ ከሉቃስ ወንጌል በምን ይለያል?
ሀ)በማቴዎስ ወንጌል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚከሱት መልስ ሰጥቷል
ለ)በማቴዎስ ወንጌል የስምዖን ቀሬናዊ ስም አልተጠቀሰም
ሐ)በሉቃስ ወንጌል ላይ ጲላጦስ እጁን አልታጠበም
መ)ሁሉም

6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያለቅሱለት ሰዎች ምን አላቸው?
ሀ)ዋጋችሁ በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ይበልጣል
ለ)ለእኔ አታልቅሱ ለራሳችሁ እና ለልጆቻችሁ አልቅሱ
ሐ)ጲላጦስን ተቃወሙ
መ)መልስ አልተሰጠም

7. በቤተመቅደስ ጀምሮ በቤተመቅደስ የጨረሰ ወንጌል የቱ ነው?
ሀ)የሉቃስ ወንጌል
ለ)የማቴዎስ ወንጌል
ሐ)የማርቆስ ወንጌል
መ)የዮሐንስ ወንጌል

8. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ የተፃፈው "ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ" በምን ቋንቋ ተጽፎ በጌታችን መስቀል ላይ ተደረገ?
ሀ)በግዕዝ፣ በጽርዕና በዕብራይስጥ
ለ)በአረማይክ፣ በሮማይስጥና በግሪክ
ሐ)በሮማይስጥ፣ በጽርዕና በዕብራይስጥ
መ)ሁሉም

9. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት በቀትር ሰዓት ላይ በምድር ላይ ከተፈፀሙት ተአምራት ውስጥ የሆነው የቱ ነው?
ሀ)ፀሐይ ጨለመ
ለ)ጨረቃ ደም ሆነ
ሐ)የቤተመቅደስ መጋረጃ ለሁለት ከላይ ወደ ታች ተቀደደ
መ)ሁሉም

10.የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ ከጲላጦስ ለምኖ የተቀበለው ዮሴፍ የምን ሀገር ሰው ነው?
ሀ)የቀሬና
ለ)የአርማትያስ
ሐ)የገሊላ
መ)የኒቅያ

11. “ይህ ሰው በእውነት ጻድቅ ነበረ"ብሎ የተናገረው ማን ነበር?
ሀ)ሄሮድስ
ለ)ጲላጦስ
ሐ)መቶ አለቃው
መ)ከገሊላ ጀምሮ የተከተሉት ሰዎች

12.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምን ቀን ወደ መቃብር ወረደ?
ሀ)በሰንበተ አይሁድ
ለ)በሰንበተ ክርስትያን
ሐ)በዕለተ አርብ
መ)በዕለተ ሐሙስ

13.ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ አገላለፅ ላይ በማርቆስ ወንጌል እና በሉቃስ ወንጌል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
ሀ)በማርቆስ ወንጌል ሁለት መላእክት እንደታዩ ሲናገር በሉቃስ ወንጌል ግን አንድ መልአክ ብቻ መሆኑን ይገልፃል
ለ) በሉቃስ ወንጌል ሁለት መላእክት እንደታዩ ሲናገር በማርቆስ ወንጌል ግን አንድ መልአክ ብቻ መሆኑን ይገልፃል
ሐ)ምንም ልዩነት የለውም
መ)መልስ አልተሰጠም

14.ከኢየሩሳሌም ወደ ስድሳ ምዕራፍ የምትርቀው ከተማ ማን ናት?
ሀ)ገሊላ
ለ)ናይን
ሐ)ናዝሬት
መ)ኤማሁስ

15.የኤማሁስ መንገደኞች በመንገዳቸው ሲጓዙ ስለምን ይወያዩ ነበር?
ሀ)ስለውሎአቸው
ለ)ስለኢየሩሳሌም መጥፋት
ሐ)ስለኤማሁስ ከተማ
መ) ስለጌታችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ መከራ እና ሞት

16.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ለእናንተ ይሁን ሲላቸው ለምን ምትሐት መሰላቸው?
ሀ)በተዘጋ ቤት ውስጥ ስለገባ
ለ)ምትሐት ያደረገ ሰው በአቅራቢያ ስላዩ
ሐ)ሰላምን ስለማይፈልጉ
መ)ሁሉም

17.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአርያም ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በየት እንዲቆዩ አዘዛቸው?
ሀ)በኢየሩሳሌም
ለ)በቅፍርናሆም
ሐ)በናዝሬት
መ)ሁሉም

18.የኤማሁስ መንገደኞች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያወቁት መቼ ነው?
ሀ)እርስ በራሳቸሁ የምትናገሩት ምንድን ነው ሲላቸው
ለ)መጻሕፍትን እየተረጎመ ሲነግራቸው
ሐ)ከእኛ ጋር እደር ብለው ሲለምኑት
መ)እንጀራን ባርኮ ቆርሶ ሲሰጣቸው

19.በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ሲሳደብ የነበረው ወንበዴን የገሰፀው ማነው?
ሀ)ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ለ)መስቀሉ ስር የነበረው መቶ አለቃ
ሐ)ተሰቅሎ የነበረው ሌላኛው ወንበዴ
መ)የሰማይ መልአክ

20. ጌታችን ነፍሱን ከመስጠቱ በፊት ምን ብሎ ተናገረ?
ሀ)አባት ሆይ ነፍሴን በአንተ እጅ አደራ እሰጣለሁ
ለ)የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው
ሐ)አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ
መ)ሁሉም